# Male circumcision & HIV prevention

## Introduction

በ 2006 ማለቂያ አካባቢ ወደ 39,5 ሚሊዮን የሚገመት ህዝብ ከኤች አይቪ ጋር ይኖር የነበረ ሲሆን 4,3 ሚሊዮን የሚሆነው ደግሞ በዚሁ አመት ተጠቂ ሆኖ ነበር። በሽታው ከመድረሱ በፊት ኤድስን ለመግታት ለሚደረገው ጥረት ቅድሚያ የተሰጠው ሲሆን ነባሮቹን የመከላከያ ዘዴዎች እና ቴክኖሎጂ ለማጠናከር አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የማስተዋወቅ ጥረት ተደርጎ ነበር። ከመጋቢት 2007 ጀምሮ የአለም ጤና ድርጅትና የተባበሩት መንግስታት HIV/AIDS (UNAIDS) የቫይረሱን ስርጭት ለመከላከል የወንዶች መገረዝ (ከቫይረሱ ተሸካሚ ሴት ወደ ወንድ) የሚተላለፈውን የኤድስ ስርጭት መግቻ ተጨማሪ ዘዴ እንደሆነ ተስማምተዋል።

የወንድ ልጅ ግርዛት የሚባለው በወንድ ብልት ጫፍ ላይ ያለውን የስጋ አካል (ሸለፈት) በቀዶ ጥግና የማስወገድ ሥራ ነው። ይህ በአለም ደረጃ ቀደምት ከሆኑት የቀዶ ጥግና ተግባራት አንዱ ሲሆን ፤ በሐይማኖት፥ በባሕል፥ በማሕበራዊ እሴት ወይንም በጤና ምክንያት ሊደረግ ይችላል። በአሁኑ ጊዜ የወንዶች ግርዛት እንደ አንዱ የኤች አይ ቪ ስርጭትን መግቻ መንገድ ሆኖ ተወስዷል። በርግጥም በኤፒዲሞሎጂ ላይ የተደረጉ ጥናቶችና የተሰበሰቡ ዐኃዞች እንደማያስረዱት፤ የወንድ ግርዛት ከተቃራኒ ፆታዎች መካከል በሚደረግ የወሲብ ግንኙነት ከሚተላልፍ የኤች አይ ቪ ወረርሽኝ ይጥብቃቸዋል።

ይሁንና የተገረዙ ወንዶች እራሳቸውን ከአደጋ ውስጥ እንደሌሉ አድርገው መቁጠር አይገባቸውም። ይህ የተሳሳተ አስተሳብ ነው!! አንዳንድ ወንዶች በመገረዛቸው ብቻ በጣም አደገኛ የሆኑ አማራጮችን ይወስዳሉ።
ይህ የተሳሳተ አስተሳብ ነው!! አንዳንድ ወንዶች በመገረዛቸው ብቻ በጣም አደገኛ የሆኑ አማራጮችን ይወስዳሉ። ይህ መግረዝ የሚሰጣቸውን ማንኛውም ጥቅሞች መና ያስቀረዋል። እዚህ ጋር በዋናነት ልንረዳው የሚገባው መገረዝ መከላከያ ሳይሆን የበሽታውን ስርጭት መግቻ መንገድ ከሆኑት አንዱ መሆኑ ነው።

### ጥናታዊ ግኝቶች

ከ1980 ጀምሮ የተደረጉ ጥናቶች እደሚያሳዩት የተገዙ ወንዶች ካልተገረዙት ያነሰ በኤች አይ ቪ መጠቃት ታይቶባቸዋል። በመጀመሪያ በደቡብ አፍሪካ በተወሰኑ ግን ደግሞ በዘፈቀድ በተመረጡ ሰዎች ላይ የተደረገው ጥናት እንደሚያሳየው 61% የሚሆን የወንዶች በሽታ ተተቂነት መቀነስ የታየ ሲሆን ይህም በወንድና ሴት የወሲብ ግንኙነት ጊዜ ነው። ይህ ጥናት በ2005 እንዲቆም ሲደረግ 60% በኤች አይ ቪ መለከፍን በተገረዙ ወንዶች ዘንድ መቀነስ አስችሎ ነበር።

በኬንያ ኪስማዩ የተደረገ ተመሣሣይ ጥናት እንደሚጠቁመው 53% ለኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ የመጋለጥ እድል በመገረዝ ምክንያት እንደሚቀንስ ተስተውሏል። ጥናቱ ታዲያ የውንዶች ግርዛት በሽታውን ወደ ሌላ ሰው በማስተላለፍ ላይ ስላለው ሁኔታ አልጠቀሰም።

በኡጋንዳ ራካኢ የተደረገ ተመሣሣይ ጥናትም 48% ለኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ የመጋለጥ እድል በመገረዝ ምክንያት እንደሚቀንስ ጠቁሞ በሽታውን ወደ ሌላ ሰው ከማስተላለፍ እንደሚከላከል ግን ጥናቱ አልጠቀሰም።

ሶስቱም በዘፈቀደ ተመርጠው በተወሰኑ ቡድኖች ላይ የትደረጉ ጥናቶች የኤች አይ ቪ ኤድስ ክስተት በተገረዙ ወንዶች ላይ (በቅርብ ክትትል ከሚደረግባቸው) በማይናቅ ሁኔታ ዝቅተኛ መሆኑ ተስተውሏል፤ ይሁንና በአጠቃላይ ባልተገረዙት ላይ (ከ07 እስከ 10 በየ100 የተገረዙ ወንዶች ላይ ተስተውሏል።

ተጨማሪ ጥናት በጆን ሆፐኪንስ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎች መሪነት የኤች አይ ቪ ስርጭት ከተገረዙ ወንዶች ወደ ሴቶች የመተላለፍ ሁኔታ ጥንአት በአሁኑ ወቅት በኡጋንዳ እየተካሄደ ነው። ውጤቱም በ2006 ይጠበቃል። ይህ ጥናት በግብረሰዶም(ወንድ ለ ወንድ)በሚደረግ የወሲብ ግንኙነትውስጥ ስላለው የበሽታ ስርጭትን በመገረዝ የመከላከል ውጤታማነት የሚገለጥው ነገር የለም።

## ባዮሎጂካል አሰራሮች

ኤክስፐርቶች እንዴት የወንዶች ግርዛት በተቃራኒ ጾታዎች መካከል በሚደረግ የወሲብ ግንኙነት ወቅት የበሽታው ተጠቂነት ሊቀንስ እንደቻለ ለመግለጽ የተለያዩ አሰራሮችን እየተጠቀሙ ይገኛሉ።

- የሸለፈቱ የውስጠኛው ክፍል በአብዛኛው በከፍተኛ ደረጃ የተሰባሰቡና በኤች አይ ቪ ለመጠቃት ምቹ የሆኑ ሴሎች ይገኛሉ። ለምሳሌም (Langerhan and CD4 + T) ሴሎች። ሸለፈቱን ማስወገድ ደግሞ የነዚህን መከማቻ ሥፍራ ማጥፋት በመሆኑ የኤች አይ ቪ ወደሰውነት የመግባት ዕድልም እንዲሁ የቀንሳል።
- ኤች አይ ቪ እና ሌሎችም ፓቶጂኖች በእርጥብ፣ ድብቅ፣ እና የውስጥ አካል በሆነ የሸለፈቱ ሥፍራ መኖር ይችላሉ። ይህንን ክፍል ማስወገዱ ታዲያ በዚህ ሥፍራ ያሉትን ፓቶጂኖች ለማስወገድ ይረዳል።
- በውሲብ ወቅት በሚፈጠረው የሸልፈት ቆዳ መፋፋቅና መቆጣት የኤች አይ ቪ ስርጭትን ያፋጥናል። ግርዛት ደግሞ የዚህን አይነት የሥርጭት መንገድ ይዘጋል።
- በተያያዥ ጥናቶች የወንዶች ግርዛት ከአነስተኛ የቂጥኝ በሽታ እና የአባልስዘር በሽቶች ስርጭት ጋር ያያይዙታል። እነዚህ በሽታዎ የብልት አልሰርን ሲያስከትሉ በኤች አይ ቪ የመለከፍም እድል ያሰፋሉ። ለምሳሌ በታንዛንያ የተደረገው ጥናት እንዳገኘው ውጤት፥ የተገረዘ ወንድ ካልተገረዘው በግማሽ ያነሰ በቂጥኝ የመለከፍ ዕድል አለው።

## ፖሊሲ አተገባበር

ከዚህ በመነሳት መገመት እንደሚቻለው ይህ ዜና የወንዶች ግርዛት ፍላጎትን በመንግሥት፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማትና በመላ ህብረተሰቡ ዘንድ በተለያዩ ሃገራት እንዲጨምር አድርጓል። በተጨማሪም ደግሞ የዚህኑ አገልግሎት መስጫ ፍላጎትን አሣድጓል። መንግስታት እንዴት አድርገው ይህን አስተማማኝ የሆነ የወንዶችን ግርዛት ከአጠቃላዩ የኤች አይ ቪ መከላከል ፕሮግራም ጋር አዋህደው እንደሚያቀርቡት በማጤን ላይ ናቸው። በተመሳሳይ ሁኔታም አስተማማኝ የሆነ የግርዛት አገልግሎት አለመኖር መዘዙ ከፍተኛ ሲሆን ጥንቃቄ ደግሞ ቅድሚያ እንዲሰጠው ግድ ይላል። የሰባዊ መብት፣ የስነምግባር፣ የገንዘበ፣ የሰው ሀይል፣ የቅድመ ጥንቃቄና ሌሎች ጉዳዮች ከታሰቡ በኋላ ግርዛትን ማስፋፋት ያሰቡ ሃገሮች የሃገሪቱን ባህልና እሴት ባገናዘበ መልኩ መተዋወቁንና መተግበሩን ሊያጤኑትና ሊያረጋግጡት ይገባል።

**ማጠቃለያ**

ይህ ጥናት የወንዶች መገረዝ ከሴቶች ወደ ወንዶች የሚተላለፈን የኤች አይ ቪ ሰርጭት አጥጋቢ በሆነ መልኩ መቀነሱን አረጋግጣአል። በወንዶች በተናጥል የሚወሰደው የመከላከል ሙከራ ጥናቱ በተደረገባቸው ምህዳሮች መሰረት (ecological, cros-sectional and cohort) እና ሶስቱ በዘፈቀደ ተመርጠው በተወሰኑ ቦታዎች የተደረጉ የተለያዩ ጥናቶች ላይ ተመሳሳይ የሆኑ የማይዋዥቁ ውጤቶች ተመዝግበዋል።

ይሁንና የወንዶች መገረዝ ሙሉ የሆነ የኤች አይ ቪ ስርጭት የመግታት ዋስትና አይሰጥም። የተገረዙ ወንዶችም ቢሆኑ በሽታውን ከበሽታው ተሸካሚ ሴት ሊያገኙት ሲችሉ ወደ ሌላ ሴትም ማስተላለፍ የችላሉ።

አስተማማኝ የሆነ የወንዶች መገረዝ ማስተዋወቅና አገልግሎትም መስጠት ሌሎቹን የኤች አይ ቪ ስርጭት መግቻ መንገዶች መተካት የማይችል ሲሆን ግን ተጨማሪ አካሄድን የጠኩማል።

- የወንዶች መገረዝ በምንም አይነት እስካሁን የሚታወቁትን የመከላከያ መንገዶች ሊተካ አይገባውም ሁሌም ቢሆን ከብዙ እንደ አንዱ የኤች አይ ቪ የመከላከያ መንገዶች ህኦኖ ማገለገል አለበት።
- በተጨማሪም የኤች አይ ቪ መከላከያ መንገዶችን የመፈለጉ ስራ በአለም አቀፍ፣ አህጉር አቀፍ፣ በሃገር አቀፍ ደረጃ ሰላለው ጠቀሜታ ለህዝቡ መነገር አለበት። ይህ አስፈላጊነቱ ወንዶች የተሳሳተ እሳቤ በመያዝ ከበሽታው የተጠበቁ የመሆን ሰሜት እና
- በአደገኛ በሆኑ የወሲብ ተግባራት ውስጥ እንዳይገቡ በሎም በመገረዛቸው ያገኙትን ጥቅም አለ አግባብ እንዳያጡት የሚመከር መሆን ይኖረበታል።
- የወንዶች ግርዛት እንደ የኤች አይ ቪ የመከላከያ ዘዴ መተቀም የሚቻለው
- የወንዶች መገረዝ ከብዙ እንደ አንዱ የኤች አይ ቪ የመከላከያ መንገዶች ሆኖ ማገለገል አለበት።
  - የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት እንዲሰጡ ማጠናከር
  - ሰብዊ መብትን ባገናዘበ መልኩ የወንዶች ግርዛትን እሳቤ ፖሊሲ በሚነደፍበት ወቅት አትኩሮት መስጠት።
  - ባህልን እና እሴትን ባገናዘበ መለኩ ማድረግ።


**Resources:**

WHO. *WHO and UNAIDS announce recommendations from expert consultation on male circumcision for HIV prevention*
http://www.who.int/hiv/mediacentre/news68/en/index.html

WHO, UNAIDS. *New Data on Male Circumcision and HIV Prevention: Policy and Programme Implications: Conclusions and Recommendations*
http://www.who.int/hiv/mediacentre/MCrecommendations_en.pdf.

WHO. *Information Package on Male Circumcision and HIV Prevention*;
http://www.who.int/hiv/mediacentre/infopack_en_1.pdf

UNAIDS, WHO. *Male Circumcision and HIV: Recent Developments;*
http://data.unaids.org/pub/FactSheet/2007/20061229_mc_fs_en.pdf?preview=true

Advocates for Youth. Written by Kathy Osborn
http://www.advocatesforyouth.org/publications/factsheet/fsmalecircumcision.htm